# ሁሉንም አንድ ገጽ ላይ የሚያሰባስብ
# አዲስ የትግል ምዕራፍ!

ኦ.ነ.ግ  ወይም የኦሮሞ ነጻ አውጭ ግንባር በሚል መጠሪያ ከሰላሳ በላይ ለዘለቁ ዓመታት ሲንቀሳቀስ የቆየው ድርጅት ከጥቂት ቀናት በፊት ስር ነቀል ወይም መሰረታዊ ሊባል በሚችል መልክ የአቋም ለውጥ በማድረግ በቀጣይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እጣ-ፋንታ ላይ ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ሚና የሚጫወት እርምጃ ወስዷል።

በታሪክ ማህደር የተቋጠረውን የድርጅቱን የበርካታ ዓመታት እንቅስቃሴ መለስ ብለን ስናገላብጥ፤  ይህን ስር-ነቀል የሆነ የአቋም ለውጥ ለመውሰድ የተኬደበት መንገድ የታለፈው ፈተናና የገጠሙ መሰናክሎች ቀላል ሊሆኑ እንደማይችሉ እንገምታለን። በመሆኑም በጽናት ቆመው ድርጅቱ ይህን አዲስና በተግባር ሊተረጎም የሚችል ራዕይ አንግቦ እንዲነሳ ላደረጉት የድርጅቱ አመራሮችና አባላቶች አድናቆታችንን ልንገልጽ እንወዳለን።

በአኳያውም ከኦነግ  ጋር በጋራ ለመስራት ይቻላል ከሚል ጽኑ እምነት በመነሳት ከአመራሮቹ ጋር ያላሰለሰ ውይይትና ምክክር በማድረግ ለአብሮነቱ እውን መሆን እርሾ ሆነው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ተቃዋሚ ድርጅቶችም ለዛሬው የኦነግ አቋም ለውጥ ባበረከቱት አስተዋጾ ሊኮሩም ሊደሰቱም ይገባል እንላለን።

የዲሞክራሲያዊነት ትልቁ መገለጫ ሃሳብን በነጻነትና ያለገድብ አንሸራሽሮ በመጨረሻም የብዙሃኑን ይሁኔታ አግኝቶ የወጣውን አመለካከት የጋራ አመለካከት አድርጎ እስከመቀበል ያለው ውስብስብና አድካሚ ጉዞ ነው። ኦነግ በዚህ ሂደት ውስጥ አልፎ የወሰደው አቋም ለድርጅቱም ሆነ ለኢትዮጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች እንቅስቃሴ አዲስ የትግል ምዕራፍ የሚከፍት ነው እንላለን።

ይህ ኦነግ ኢትዮጵያዊነትን አድምቆ፤ የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ ጥያቄና አላማ እንደሌለው አስረግጦ ያወጣው የአቋም መግለጫ የተሰጠው ፤ ዘረኛው የወያኔ መንግስት ኦነግንና ሌሎችንም ቁርጠኛ ተቃዋሚዎች በሽብርተኝነት ፈርጆ የጥቃት ዘመቻ በከፈተበት ወቅት መሆኑ በራሱ፡- ገዢው ፓርቲ  እለት ተእለት በሚወሰድው የጭንቀት እርምጃ ውድቀቱን እያፋጠነ መሆኑን የሚያረጋግጥ ይመስለናል።

ከ20 ዓመታት በፊት በሽግግር መንግስት ምስረታ ላይ የተተከለው የጎሳ ፖለቲካ መርዝ፤ ከጅምሩ አንስቶ  ለበርካታ ንጹሃን ዜጎች ህይወት መጥፋት ምክንያት መሆኑን ስናስታውስ ሀዘናችን ይከብዳል።ለዚህ አስከፊ የታሪክ ገጽታ ዋናው ተጠያቂ ወያኔ መራሹ መንግስት ቢሆንም፡- እንደ ዜጋ እያንዳንዳችን፤ እንደ ድርጅትም እያንዳዱ ተቃዋሚ ድርጅት በገዢው ፓርቲ የተለኮሰውን የጥፋት እሳት ለመገደብ በሚችልበት ጎዳና ለመጓዝ ባለመፍቀዱ ለጥፋቱ እሳት 20 አመታት መዝለቅ የበኩሉን አስተዋጾ ማድረጉን መካድ አይቻልም።

ይሁንና ከትናት ተምሮ፤ በዛሬ ሞክሮ፤ ለነገ ደግሞ መክሮ ማደር የውጤታማነት ዋንኛ መርህ መሆኑን የተገነዘቡ ወገኖች ከትናት ስኬት አልባ ጉዞ ተምረው፤ ዛሬ ሞክረው፤ ለነገ የሚያዋጣውን መንገድ መክረው፤ የጎሳ ፖለቲካ መርዝ ዳግም ላይጎዳን ማርከሻውን **“ኢትዮጵያዊነትን”** ይዘናል ብለውናል። ዋናው መማሩ ነውና እኛም እሰየው ብለናል።

ዛሬ የብሄር ድርጅቶች በጠቅላላው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ስዕል ላይ የሚታዩ የሚዳሰሱ አካሎች መሆናቸውን ወደድንም ጠላንም ልንቀበለው የሚገባ እውነት ነው። የምንታገለው አገራዊ ራዕይን የሚያደበዝዘውን የጎሳ ፖለቲካን እንጂ ድርጅቶቹን አይደለም ሲባል ለቆየው አመለካከት እውነተኝነት ትልቁ መገለጫ ዛሬ በኦነግ የተወሰደው የአቋም ለውጥ ነው፡፡

ኦነግ ዛሬም ለኦሮሞ ህዝቦች መብት መከበር የቆመ ድርጅት ነው። ይሁንና የኦሮሞ ህዝብ መብት ሊከበር የሚችለው የመላው ኢትዮጵያዊ ሕዝብ መብት ሲከበርና እንደ ሃገርም ኢትዮጵያ የምትባለው ሃገር ልዋላዊነቷ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑን

በመቀበል የጎሳ ፖለቲካ ከሚፈጥረው አጣብቂኝና ጠባብ ጎዳና ተመንጥቆ ወጥቷል። እሰየው የሚያሰኘውም ይህ ነው፤ የጋራ አገራዊ ራዕይን ማስቀደም።

ጸረ ሃገርና ጸረ ሕዝብ የሆነውን የወያኔ መንግስት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለመጣል እየተንቀሳቀሱ ያሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች ዛሬ ኦነግ በወሰደው የአቋም ለውጥ ከፍተኛ እርካታ እንደሚሰማቸው እምነታች ነው። ቢያንስ ቢያንስ **በቃል የሚነግሩንን በኦፊሴላዊ መግለጫ ለምን አያረጋግጡም?** እያልን ጥያቄ ስናነሳ ለነበርን ወገኖች በቂ ምላሽ አግኝተናል።በኛ ዕምነት በኦነግ የአቋም ለውጥ የሚደናገጠው ወያኔ ብቻ ነው።

ከዚህ በኋላ ከተቃዋሚ ወገን ነን የሚሉ ነገር ግን፤ በማይነጥፍ ተጠራጣሪነት ቃላትን እየሰነጠቁ በጥያቄ ናዳ የሚያጨናንቁ ወገኖች የሚኖሩ አይመስለንም። ቢኖሩም መኖራቸውን ለማመልከት አቅም ያለው ህልውና አይኖራቸውም ። የስካሁኑ ጥያቄ ተመልሷልና፡-

የኦነግ የአቋም ለውጥ አዲስ የትግል ምዕራፍ ከፍቷል ስንል ያለምክንያት አይደለም። ድርጅቱ ይዞት የቆየው "የኦሮሞ ሕዝብ ነጻነት" የሚለው መርህ ለበርካታ የህብረት ጉዞዎች መጨናገፍ ምክንያት በመሆኑና ፤ ይህ ግዙፍ የህዝብ ተዋጾ ያለው ብሄርን የሚወክል ድርጅት ኢትዮጵያዊ ራዕይን አንግቦ መነሳቱ ለጋራ ትግሉም ሆነ ለህዝባችን አብሮነት የሚጫወተውን ጉልህ ሚና ከግምት በማስገባት እንጂ።

በኛ እምነት ይህ አዲስ የትግል ምዕራፍ ጸረ ሃገር የሆነውን የአቶ መለስ መንግስት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ለመጣል እታገላለሁ የሚለው ወገን ሁሉ ቅሌን ማቄን ሳይል ወደ አንድ ገጽ ላይ የሚያሰባስብ መልካም አጋጣሚ ይመስለናል።

ለዚህም ዕውን መሆን በተለይ በዲያስፖራ የሚገኘው ወገን ትልቅ ሚና ሊጫወት እንደሚችልና እንደሚገባውም እምነታችን ነው። ይህ የኦነግ መግለጫ የጎሳ ፖለቲካን አከርካሬ የሰበረ መሆኑን የምናረጋግጠው ሁሉም ኢትዮጵያዊ የቋንቋና የዘር አጥሩን በመስበር በጎሳ ፖለቲካ ሳቢያ ደብዝዞ የቆየውን አብሮነት ለማድመቅ ሲችል ነውና እንደዜጋ ሁሉም የሚጠበቅበትን ያደርግ ዘንድ ግድ ነው እንላለን።

በዚህ አጋጣሚ ኦነግ አዲሱን ራዕይ ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ በሜኒሶታ ባደረገው ስብሰባ ጥሪ ያስተላለፈው ለኦሮሞ ተወላጆች ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ መሆኑ የነገውን የእንቅስቃሴ ይዘት አመላካች መሆኑን ለማስታወስ እንሻለን። በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ የሚደረግ የጋራ እንቅስቃሴ።

በርግጥ ብዙ ጅምር የአብሮ መስራት ውሎች ሲጨናገፉ በመታዘበቻን ዛሬም በኦነግ የአቋም ለውጥ ላይ ሙሉ እምነታችንን ለመጣል ግዜ እንደሚወስድብን ግልጽ ነው። ይህም ከ20 ዓመት የትግል ቆይታ ልምድ የቀሰምነው በመሆኑ ጤነኛ አተያየት ነው እንላለን። ይሁንና ጅምሩ ሊበረታታ የሚገባውና ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መልክ የተወሰደ የአቋም ለውጥ መሆኑን ከግምት በማስገባት ቅጥ ካጣ ጥርጣሬና ስጋት ተላቀን የተወሰደውን የአቋም ለውጥ ልናበረታታና ልንደግፈው ይገባል እንላለን።

በመሆኑም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሙብትና ነጻነት ቆመናል የምንል ወገኖች ሁሉ በኦነግ የተወሰደውን ታላቅና አገራዊ ራዕይ ያነገበ "የአቋም ለውጥ" በቀና መንፈስ ተቀብለን የጋራ ክንድንና ሕብረትን ግድ የሚለውን **ለኢትዮጵያና ለህዝቦቿ ነጻነት የሚደረገውን ትግል ለማጠናከር እንነሳ!!** በማለት በኦነግ አዲስ ራዕይ ላይ ያለንን አቋም ያንጸባረቅንበትን ርዕሰ አንቀጽ በዚሁ እንቋጫለን!!!

**ታህሳስ 24 2004 ዓ.ም**

**የቋጠሮ ዝግጅት ክፍል**
**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**